amharisch
amharique
amarico
Amharic

# ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ

## የት አደጋው አለ

## የት ደግሞ የለም

### መረጃ ለወንዶች

ኤድስ አደገኛ የሆነ በሽታ ነው … እስከዛሬ ድረስ የማይድን በሽታ ነው። ኤድስ በዓለም ሁሉ የተስፋፋ ሲሆን በስዊዘርላንድም እንዲሁ ችግር ነው። የኤድስ መንስዔ ኤች.አይ. ቫይረስ ነው (ባጭሩ ኤች.አይ.ቪ. ይባላል)። ኤች.አይ.ቪ. በረጅም ዓመታት ውስጥ የሰውነት በሽታን የመከላከል አቅም ያዳክማል። እናም ወደፊት አንድ ወቅት ላይ ሰውነት ለብዙ በሽታዎች ይጋለጣል። በዚህ ምክንያት በኤች.አይ.ቪ. የተያዙ ሰዎች ሕመማቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጠና ይሄዳል። ይህም ኤድስ ይባላል።

መከላከያ: ኤች.አይ.ቪ. ወደ እስዎ ሊተላለፍ የሚችለው በምን ሁኔታ እንደሆነ ይህ ጽሑፍ ያብራራልዎታል። በተጨማሪም ጽሑፉ እራስዎንና እንዲሁም የሴት ወይም የወንድ የፍቅር ጓደኞችዎን ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እንዳይጋለጡ እንዴት አድርገው ሊከላከሉ እንደሚችሉ ያስረዳዎታል!

ኤድስ አይድንም፣ … ነገር ግን ኤች.አይ.ቪ. በሰውነት ውስጥ የሚያደርገውን የስርጭት ፍጥነት ለመቀነስ የሚረዱ መድሃኒቶች አሉ። ስዊዘርላንድ ውስጥ — አንድ ሰው የመኖሪያ ፈቃድ ይኑረው አይኑረው ምንም ሚና ሳይጫወት — ሁሉም ሰው ውጤታማ የሆነ ሕክምና የማግኘት መብት አለው። ሕክምና በጊዜው መጀመር ይኖርበታል። ነገር ግን በቫይረሱ መያዙን የማያውቅ ሰው፣ ሕክምና ቢጀመርበት በጣም አመርቂ ውጤት የሚያስገኘውን ትክክለኛውን ጊዜ ሳይጠቀምበት ያሳልፈዋል። ስለዚህ የቫይረሱ ተሸካሚ መሆንንና አለመሆንን ለይቶ ማወቅ እጅግ ጠቃሚ ነው። ለይበልጥ መረጃ በእዚህ ጽሑፍ በስተጀርባ ያለውን ይመልከቱ።

LOVE LIFE STOP AIDS

www.lovelife.ch

# አደጋ

ኤች.አይ.ቪ. ካለኮንዶም በሚፈጸም የግብረ ሥጋ ግንኙነት ይተላለፋል። ከኤች.አይ.ቪ./ኤድስና ከሌሎች ተላላፊ በሽታዎች ራስን ለመጠበቅ ዋናው መከላከያ ኮንዶም ነው።

## በፊንጢጣ የሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ካለኮንዶም





●●● በጣም ከፍተኛ አደጋ

ለሁለቱም የወሲብ ጓደኞች፣ የወንድ የዘር ፈሳሽ ባይኖርም እንኳን

■ መከላከያው፦

ኮንዶምና በቂ ማለስለሻ

## በሴት ብልት የሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ካለኮንዶም



●●○ ከፍተኛ አደጋ

ለወንድም ለሴትም፣ የወንድ የዘር ፈሳሽ ባይኖርም እንኳን

■ መከላከያው፦ ኮንዶም

## በአፍ የሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ካለመከላከያ



●○○ አደጋው እንዳለ ነው

■ መከላከያው፦ ከአንድ ሴት ጋር በወር አበባዋ ጊዜ ወሲብ ነክ ድርጊት አለመፈጸም።

የወንድ የዘር ፈሳሽ ወደ አፍ ውስጥ አለማስገባት!

የወንድ የዘር ፈሳሽ አለመዋጥ!

# የኮንዶም አጠቃቀም እንደዚህ ነው

1. የኮንዶሙ ማሸጊያ ያልተቀደደና ያልተበላሸ መሆኑን ያረጋግጡ።




2. የኮንዶሙን ማሸጊያ በጥንቃቄ ትክክለኛው ቦታ ላይ ቀዶ መክፈት፤ ኮንዶሙን ማውጣት።

3. ያልተገረዙ ከሆነ የብልትዎን ጫፍ የሚሸፍነውን ቆዳ ወደኋላ ሰብስቦ ማድረግ።



4. የተጠቀለለውን ኮንዶም በአውራ ጣትና በሌባ ጣት በመያዝ ብልትዎ ጫፍ ላይ ማስቀመጥ። የኮንዶሙ ቀለበት ወደ ውጭ ያሳያል።



5. ኮንዶሙን ወደታች መተርተር። ኮንዶሙ በቀላሉ መተርተር አለበት። በቀላሉ መተርተር ካልተቻለ ግን ስለጠበበ ወይም ስለሰፋ ነው ወይም ደግሞ የኮንዶሙ ቀለበት ወደ ውጭ ማሳየት ሲገባው ወደ ውስጥ ያሳያል።



6. ከእርካታ በኋላ ብልቱ እንደገና ተመልሶ ከመተኛቱ በፊት ከኮንዶሙ ማውጣት፤ በዚህ ወቅት ኮንዶሙ ተንሸራቶ እንዳይወልቅ ከብልቱ ጋር ከሥሩ ጠበቅ አድርጎ መያዝ ያስፈልጋል።

በነገራችን ላይ፦ ግብረ ሥጋ ግንኙነት ከመፈጸሙ በፊት ከሴት ብልት ውስጥ የሚገባ ለሴት የሚሆን ፌሚዶን (Femidom®) የሚባል ኮንዶም አለ። ይሁንና ግን ለወንድ የሚሆነው ኮንዶም አጠቃቀሙ ቀላል ሲሆን ዋጋውም ረከስ ይላል።

# ተጨማሪ የቫይረሱ መተላለፊያ መንገዶች

## ኤች.አይ.ቪ. ካለባት እናት ወደ ልጇ



በእርግዝና ወቅት፣ በወሊድ ጊዜና በጡት ማጥባት ወቅት።

●●● በጣም ከፍተኛ አደጋ

■ መከላከያ፦ የኤች.አይ.ቪ. ምርመራ አድርጋ የባይረሱ ተሸካሚ መሆንዋ የተረጋገጠ እርጉዝ ሴት፣ ተስማሚ የሆነ የሕክምና ክትትል ተደርጎላት ቫይረሱ ወደ ልጇ እንዳይተላለፍ ሊደረግ ይችላል።

## ድራግ መውሰድ



ድራግ ለመውሰድ መውጊያ መርፌ ጋንና መውጊያ መርፌ በጋርዮሽ መጠቀም።

●●● በጣም ከፍተኛ አደጋ

■ መከላከያ፦ ንጹህ የሆኑ መሣሪያዎች (መውጊያ መርፌ ጋን፣ መውጊያ መርፌ፣ ማጥለያ፣ ጥጥ፣ ማንኪያና ውሃ)፤ እነዚህን መሣሪያዎች በጋርዮሽ አለመጠቀም።
እነዚህ ጥንቃቄዎች ካልተደረጉ፣ በተጨማሪ በጣም ከፍተኛ በሆነ ደረጃ አደገኛ ለሆነው ሄፓቲቲስ ሲ ቫይረስ ተብሎ ለሚታወቀው የጉበት በሽታ (ኤች.ሲ.ቪ/HCV) መጋለጥን ያስከትላል።

## ቀዶ ሕክምና / ግርዛት

●●● በጣም ከፍተኛ አደጋ

ቀዶ ሕክምና፣ ግርዛት፣ ንቅሳት ወዘተ. ለማከናወን ሥራ ላይ የሚውሉ መሣሪያዎች (የመድሐኒት መውጊያ መርፌ ጋንና መውጊያ መርፌ፣ ቢላዋ ...) ጀርም አልባ ሆነው ሳይጸዱ ለብዙ ሰዎች መገልገያ ከሆኑ ኤች.አይ.ቪ. ሊተላለፍ ይችላል። ከኤች.አይ.ቪ. ነጻ ለመሆናቸው ተመርምረው ያልተረጋገጡ የደም ምርቶችን በመውሰድም እንደዚሁ ቫይረሱ ሊተላለፍ ይችላል።

○○○ አደጋ የለም

ስዊዘርላንድ ውስጥ እውቅና ባላቸው የሕክምና ባለሙያዎች በሚሰጡ የሕክምና አገልግሎቶች ቫይረሱ ተላልፎ አያውቅም።

# ለቫይረሱ የመጋለጥ አደጋ የለም




በሥራ ቦታ — መጸዳጃና መታጠቢያ ክፍሎች




በማነጠስ፣ በመሳል



እጅ ለእጅ በመጨባበጥ፣ በመዳሰስ፣ በመተቃቀፍ



በጋርዮሽ በአንድ የምግብ ሰሃን በመብላት፣
በጋርዮሽ በአንድ ብርጭቆ በመጠጣት



በነፍሳት በመነከስ፣
በመዋኛ ቦታ፣ በዛውና

ይህ ዝርዝር የሚያሳየው፦ በዕለታዊ ኑሮ ለቫይረሱ የመጋለጥ አደጋ አይኖርም። ስለእዚህ ኤች.አይ.ቪ. ያለባቸው ሰዎች ቫይረሱን ወደ ሌላ ሰው ያስተላልፋሉ ብሎ መፍራት ብሎም ከማህበራዊ ኑሮ ወይም ከሥራ ዓለም ለማግለል መሞከር ምንም ምክንያት የለውም።

በሚከተሉት ሁኔታዎችም እንደዚሁ አደጋው የለም፦



በመሳሳም ወይም እርስ በርስ በእጅ ወሲብ ነክ ድርጊት በመፈጸም፣
ጥንቃቄ የተሞላበት የግብረ ሥጋ ግንኙነት በመፈጸም (በኮንዶም)

# ሌሎች በወሲብ የሚተላለፉ የአባለዘር በሽታዎች

የግብረ ሥጋ ግንኙነት በመፈጸም ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በተጨማሪ ሌሎች በሽታዎች ሊተላለፉ ይችላሉ፦ ለምሳሌ ጨብጥ፣ ኸርፐስ፣ ቂጥኝ፣ ክላሚዲን ወይም ደግሞ ሄፓቲቲስ ቢ የሚባል የጉበት በሽታ።

## ምልክቶችና ሕመሞች → ወደ ሐኪም ይሂዱ!

እነዚህ በሽታዎች በአብዛኛው የተወሰኑ የሕመም ዓይነቶችን ያመጣሉ።

- የተለያየ መጠንና ቀለም ያለው ፈሳሽ ከመሽኛ ቱቦ/ከወንድ ብልት ይወጣል
- በሽንት ጊዜ የማቃጠል ስሜት፣ ከመሽኛ ቱቦ አካባቢ ማሳከክ
- በቆለጥ አካባቢ ማመምና እብጠት
- ብልት ወይም ቆለጥ አካባቢ የቆየ ቁስል፣ እባጭ፣ እኸ ቋጠሮ፣ ሽፍታና እከክ
- የታችኛው የሆድ ዕቃ አካባቢ ሕመም
- በመፀዳዳት ወቅት የሕመም ስሜት
- እሬብን ጫን የሚያደርግ ሕመም፣ ከእሬብ የሚወጣ ፍሳሽ
- ፊንጢጣ ላይ እባጭ፣ እኸ ቋጠሮ

የእዚህ ዓይነት የጤና መታወክ ካለብዎት በአፋጣኝ ወደ ሐኪም ይሂዱ!

ልብ ይበሉ፦ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ወደ እነዚህ ሕመሞች አያመራም!
ነገር ግን በኤች.አይ.ቪ ምርመራ ብቻ ነው አንድ ሰው በቫይረሱ መያዙን ወይም አለመያዙን በእርግጠኝነት ማወቅ የሚችለው።

## የሚያስከትሉት መዘዝ

ብዙዎቹ እነዚህ በሽታዎች በጊዜ ከታወቁ በሕክምና ሊድኑ ይችላሉ። ሕክምና ካልተደረገ ግን የሚያስከትሉት መዘዝ (ካንሰር፣ ምክነት) ከባድ ከመሆኑም በላይ ለኤች.አይ.ቪ የመጋለጥ አደጋም እንዲሁ በጣም ከፍ ያለ ይሆናል።

## መከላከያ፦ በኮንዶም

ከእነዚህ ተላላፊ የአባለዘር በሽታዎች ራስን ለመጠበቅ፣ በሴት ብልት፣ በፊንጢጣና እንዲሁም በአፍ ለሚፈጸም ወሲብ ኮንዶም መጠቀም እጅግ በጣም ጥሩ የሆነ መከላከያ ነው።
በተለይም ከሴትኛ አዳሪዎች ጋር በአፍ በሚፈጸም ወሲብ ኮንዶም ሁልጊዜ መጠቀም እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው።

# ኮንዶምና ማለስለሻን በሚመለከት መረጃ

## መከላከያ፦

ኮንዶም ከኤች.አይ.ቪና ከሌሎች ተላላፊ የአባለዘር በሽታዎች ይከላከላል። ኮንዶም እንደ የፅንስ መከላከያ ሆኖም ሊያገለግላል ይችላል።

## ጥራት ያለው ኮንዶም / ልክዎን ይምረጡ

«ok» የሚል የምርት ጥራት ደረጃን የሚያሳይ ምልክት ያለበትን ኮንዶም ብቻ ይጠቀሙ። ይህም በየሱፐር ማርኬቱ፣ ድሮገሪዎችና ፋርማሲዎች ይገኛል።

የተለያየ መጠንና መልክ የላቸው ኮንዶሞች ይገኛሉ። ለእርስዎ ልክ የሚሆነውን ኮንዶም ይምረጡ። ጠባብ ከሆነ ይፈነዳል ወይም ይቀዳዳል፤ ሰፊ ከሆነ ደግሞ ስለማይዝ ይወልቃል። ለእስዎ ልክ የሚሆነውን ኮንዶም ለማግኘት ለምሳሌ ወደ እዚህ የኢንተርኔት አድራሻ ሄደው ይመልከቱ፦ www.mysize.ch

## የአገልግሎት ጊዜው ያላለፈበት / የማስቀመጫ ቦታ

የሚጠቀሙበት ኮንዶም የአገልግሎት ጊዜው ያላለፈበት ለመሆኑ ማሸጊያው ላይ የተጻፈውን ቀን አይተው ያረጋግጡ። ኮንዶሙን ከብርሃንና ሹል ከሆነ ነገር ያርቁ።

## ማለስለሻ

አስፈላጊ ከሆነ በዛ አድርገው ቅባት አልባ፣ ከውሃ የተሰራ ማለትም በውሃ የሚሟሟ ማለስለሻ (ብልትን በቀላሉ ለማስገባት የሚረዳ፣ እርጥበት ሰጭ ጌል) ይጠቀሙ። ይህንንም ከሱፐር ማርኬቶች፣ ከድሮገሪዎችና ከፋርማሲዎች ማግኘት ይቻላል። ቫዘሊን፣ የሰውነት ቆዳ ማለስለሻ ማለትም ቦዲሎሽን፣ የመታሻና የምግብ ዘይት በፍጹም እንዳይጠቀሙ።

ሁለት ኮንዶም አንዱን በሌላው ላይ ደርበው በፍጹም እንዳይጠቀሙ!

## ምን ማድረግ ይችላሉ ...

ወሲብ ሲፈጽሙ ኮንዶሙ ቢቀደድ ወይም ቢፈነዳ እናም የወሲብ ጓደኛዎ ሴት ወይም ወንድ በእርግጠኝነት የኤች.አይ.ቪ ተሸካሚ ወይም ደግሞ የኤች.አይ.ቪ ተሸካሚ ለመሆን ያላት ወይም ያለው እድል በጣም ከፍተኛ ቢሆን?
በጣም ቢዘገይ በሚቀጥለው ቀን ወደ አንድ የኤድስ ድጋፍ ሰጭ ድርጅት ወይም ሆስፒታል ሄደው የምክር አገልግሎት ያግኙ፤ በዚህ ሁኔታ ምን ማደረግ እንደሚቻል የመስኩ ባለሙያዎች ያብራሩልዎታል። ከአደጋው ለመዳን እድል ይኖርዎታል፤ ቀላልና ካለምንም ጥርጥር ፍቱን የሆነ ሕክምና ግን የለም።

# ያለብዎት ኀላፊነት!

ወሲብ በሚፈበጸምበት ጊዜ ኮንዶም መጠቀም ግድ ነው። ኮንዶም እስዎንና እንዲሁም ከእስዎ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚፈጽሙትንም ሰዎች ጭምር ከአደጋ ይጠብቃል። እባክዎን ኀላፊነት ይሰማዎት - ሁልጊዜ ኮንዶም ይኑርዎት፤ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሲፈጽሙ ይጠቀሙበት!

አንድ ሰው በቸልተኛነት ኮንዶም ባለመጠቀሙ ምክንያት ወደ የሴት ጓደውኛው ኤች.አይ.ቪ. ቢያስተላልፍ፣ በወንጀል ተከሶ ምንአልባትም የብዙ ዓመታት የእስር ቤት ቅጣት ሊፈረድበት ይችላል!

## በነገራችን ላይ

የግብረ ሥጋ ግንኙነት ካለኮንዶም ሲፈጽሙ የቆዩ ከሆነና እስካሁን ድረስ ግን ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ካልያዘዎት፣ ሌላ ነገር ሳይሆን እድለኛ ስለሆኑ ብቻ ነው። ምን ጊዜም ቢሆን ኮንዶም ሳይጠቀሙ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም፣ የሚያስከትለው ለቫይረሱ የመጋለጥ አደጋ ትልቅ ነው!

ዝቅ ሲል የተጠቀሱት ሦስት መስፈርቶች ከተሟሉ ብቻ ነው ካለምንም አደጋ ኮንዶም ሳይጠቀሙ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም የሚችሉት፦

- ከፍቅር ጓደኛዎት ጋር በቋሚና በጽኑ ትስስር የሚኖሩ ከሆነ
- እስዎም ሆኑ የሴት ወይም የወንድ ጓደኛዎት የምትፈጽሙት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከእርስ በርሳችሁ ጋር ብቻ ከሆነ
- ሁለታችሁም — በጣም የሚመረጠው አብራችሁ በአንድ ላይ — ምርመራ አድርጋችሁ፣ ሁለታችሁም ከኤች.አይ.ቪ. ነፃ መሆናችሁ የተረጋገጠ ከሆነ ነው።

እስዎ እነዚህን መስፈርቶች ያሟላሉ? እርግጠኛስ ነዎት?

© Bundesamt für Gesundheit, Aids-Hilfe Schweiz, 2006
ጽሑፍ/ዝግጅት፦ Lukas Meyer ትርጉም፦ Mesfin Ayalew, www.amharic-company.de
ግራፊክ ዲዛይን፦ DVISIONS Herrmann Germann Bienz / www.alscher.ch
ኅትመት፦ Mengis Druck und Verlag AG, Visp የእትም ብዛት፦ 2500

# ተጨማሪ መረጃና የምክር አገልግሎት

## የምክር አገልግሎት

በየትኛውም የኤድስ ድጋፍ ሰጭ ድርጅት፦ በግንባር ቀርበው ወይም በስልክ ደውለው መጠየቅ ይችላሉ። ፍላጎትዎ ከሆነም ስምዎን ሳይጠቅሱ የምክር አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ።
ወደ ሐኪም በመሄድ፦ ምንም ሳያመናቱ ስለ ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ያለዎትን ጥያቄዎች ለሐኪሙ ወይም ለሐኪሟ ያቅርቡ። ሐኪሞች ከታካሚዎቻቸው የሚያገኙትን መረጃ በምስጢር የመያዝ ጥብቅ ኀላፊነት አለባቸው።

## የቋንቋ ችግር

የምክር አገልግሎት በየትኛዎቹ ቋንቋዎች እንደሚሰጥ ያጣሩ። የሚያስተረጉምልዎን ሰው ራስዎ አፈላልገው ይዘው መምጣት ይኖርብዎት ይሆናል።(አስተርጓሚ ለማግኘት ወደ እዚህ የኢንተርኔት አድራሻ ሄደው ይመልከቱ፦ www.eka-cfe.ch/d/Doku/vermittlungsstellen.pdf ወይም ከኤድስ ድጋፍ ሰጭ ድርጅት መረጃ ለማግኘት ይቻላል)።

## ተጨማሪ መረጃ

የእዚህን ጽሑፍ ተጨማሪ ቅጅዎችንም ይሁን ሌሎች ስዊዘርላንድ ውስጥ የጤንነት ነክ ጉዳዮች ላይ የተዘጋጁ ጽሑፎችን፣ ዝቅ ብለው በተጠቀሱት አድራሻዎች በኩል ማግኘት ይችላሉ፦
Aids-Hilfe Schweiz, Postfach 1118, 8031 Zürich
ጽሑፍ ለማዘዝ፦ ሥልክ፦ 044 447 11 13, ፋክስ፦ 044 447 11 14,
ኢሜል፦ shop@aids.ch, የኢንተርኔት አድራሻ፦ www.shop.aids.ch
ሌሎች መረጃዎች ለማግኘት፦ ሥልክ፦ 044 447 11 11, ፋክስ፦ 044 447 11 12,
ኢሜል፦ aids@aids.ch, የኢንተርኔት አድራሻ፦ www.aids.ch

በእስዎ ቋንቋ የተዘጋጁ መረጃዎች ይኖሩ እንደሆነ እንደሆነ የኤድስ ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶችን ይጠይቁ፤ ወይም ወደ እዚህ የኢንተርኔት አድራሻ ሄደው መጣጥፎችን ይፈልጉ፦ **www.migesplus.ch**

ይህ ጽሑፍ ዝቅ ሲል በተዘረዘሩት ቋንቋዎች ተተርጉሞ ለንባብ ቀርቧል፦

albanisch, albanais, albanese, Albanian
amharisch, amharique, amarico, Amharic
arabisch, arabe, arabo, Arabic
deutsch, allemand, tedesco, German
englisch, anglais, inglese, English
französisch, français, francese, French
italienisch, italien, italiano, Italian
portugiesisch, portugais, portoghese, Portuguese
rumänisch, roumain, rumeno, Romanian
russisch, russe, russo, Russian
serbisch/kroatisch/bosnisch, serbe/croate/bosniaque, serbo/croato/bosniaco, Serbian/Croatian/Bosnian
somalisch, somalien, somalo, Somali
spanisch, espagnol, spagnolo, Spanish
suaheli, swahili, swahili, Swahili
tamilisch, tamoul, tamil, Tamil
thai, thaï, thai, Thai
türkisch, turc, turco, Turkish

# በቫይረሱ ተይዣለሁ ወይስ ከቫይረሱ ነፃ ነኝ?

አንድ ሰው የኤች.አይ.ቪ. ተሸካሚ መሆኑን ካወቀ ብቻ ነው ትክክለኛው ጊዜ ሳያልፍበት ሕክምናውን ሊጀምር የሚችለው።

## የኤች.አይ.ቪ. ምርመራ

የኤች.አይ.ቪ. ተሸካሚ መሆንዎንና አለመሆንዎን በእርግጠኛነት ለማወቅ የሚረዳዎት የኤች.አይ.ቪ. ምርመራ ሲያደርጉ ብቻ ነው። ቫይረሱ ወደ ሰውነት ውስጥ ከገባ በኋላ መጀመሪያ ወቅት ላይ በአብዛኛው የጤና መታወክ አይኖርም። ቫይረሱ ወደ ሰውነት ውስጥ መግባቱን በግልጽ የሚያመለክቱ የሕመም ምልክቶች የሉም፤ ኤች.አይ.ቪ. መጀመሪያ ላይ አይታይም። ጥንቃቄ የጎደለው (ለምሳሌ ካለኮንዶም) የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከተፈጸመ ከሦስት ወራት በኋላ የሚደረግ ምርመራ ነው በመሠረቱ ትርጉም የሚኖረው። ከእዚህ የጊዜ ገደብ በኋላ የሚደረግ ምርመራ ግን በእርግጥ አስተማማኝ የሆነ ውጤት ይሰጣል። ቫይረሱ ከተገኘብዎት ግን በእነዚህ የመጀመሪያ ሦስት ወራት ውስጥም ቢሆን ወደ ሌላ ሰው ሊያስተላልፉት ይችላሉ።

## የምርመራው ምስጢራዊነት

ወደ አንድ ትልቅ ሆስፒታል ወይም ቀጥታ ወደ ላቦራቶሪ (የሽንት፣ የደም ወዘተ. ምርመራ የሚካሄድበት ተቋም) ሄደው ስምዎን ሳይጠቅሱ ሊመረመሩ ይችላሉ። በእዚህም ምክንያት መመርመርዎንም ይሁን ምን ዓይነት የምርመራ ውጤት እንዳገኙ ሊያውቅ የሚችል ማንም ሰው አይኖርም።

## ቅድመ ምርመራ የምክር አገልግሎት

ምርመራ ከማድረግዎ በፊት እንደምንም ብለው የምክር አገልግሎት ያግኙ፦ ከአንድ የኤድስ ድጋፍ ሰጭ ድርጅት፣ ከሆስፒታል፣ ከላቦራቶሪ ወይም ከራስዎ ሐኪም። ወይም ደግሞ እንደ ሁኔታው የእስዎን የስደተኛነት ጉዳይ የሚከታተለውን መሥሪያ ቤት ባልደረባ ያነጋግሩ።

(ማንነትዎን ሳይገልጹ) ስለ አድርሻዎች፣ ስለ ጽሑፎች፣ ስለ የምርመራ መዕከሎች ወዘተ. መረጃ ለማግኘት እንዲሁም እንዲላክልዎት ከፈለጉ ለማዘዝ፣ የስልክ ቁጥርና የኢንተርኔት አድራሻ እነሆ፦ 044 447 11 11 / www.aids.ch

ወይም በቀጥታ፦